ሕብረት ባንክ
Hibret Bank
በሕብረት እንደግ!

hibretbank.com.et

# የስብሰባ ጥሪ

# ለሕብረት ባንክ አ.ማ. ባለአክሲዮኖች በሙሉ

## የባለአክስዮኖች 28ኛ መደበኛ እና 14ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤዎች የስብሰባ ጥሪ

በኢፌዲሪ ንግድ ሕግ አንቀጽ 366 (1)፣ 367 (1)፣ አንቀጽ 370 እንዲሁም በአክሲዮን ማኅበሩ መመሥረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 14 መሠረት፣ ሕብረት ባንክ አ.ማ. የባለአክስዮኖች 28ኛ መደበኛ እና 14ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤዎቹን **ሰኞ፣ ሕዳር 29 ቀን 2018 ዓ.ም. ከጠዋቱ 2፡00 ሰዓት ጀምሮ በሸራተን አዲስ ሆቴል** ስለሚያካሄድ፣ የባንኩ ባለአክሲዮኖች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተጠቀሰው ቀን፣ ሰዓትና ቦታ በስብሰባው ላይ እንዲገኙ የባንኩ የዲሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን ያቀርባል።

## 1. ማህበሩን የሚመለከቱ ዋና ዋና መረጃዎች

| | | |
|---|---|---|
| 1.1. | የአክስዮን ማኅበሩ ስም | ሕብረት ባንክ አ.ማ |
| 1.2. | የስራው አይነት | የባንክ ስራ |
| 1.3. | የአክሲዮን ማህበሩ አድራሻ | አዲስ አበባ፣ ልደታ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 07፣ የቤት ቁጥር አዲስ |
| 1.4. | የባንኩ ድረ-ገጽ | http://www.hibretbank.com.et |
| 1.5. | የአክሲዮን ማህበሩ የምዝገባ ቁጥር | LLB/006/98 |
| 1.6. | የአክስዮን ማኅበሩ የተፈረመ ዋና ገንዘብ ብር (ካፒታል) | 11,665,497,000 |
| 1.7. | የአክስዮን ማኅበሩ የተከፈለ ዋና ገንዘብ ብር | 8,120,629,559.19 |

## 2. የ28ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች

| | |
|---|---|
| 2.1 | የስብሰባውን አጀንዳ ማጽደቅ፣ |
| 2.2 | የአክሲዮን ዝውውር ማጽደቅ፣ |
| 2.3 | እ.ኤ.አ የ2024/2025 በጀት ዓመት የዲሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት ማድመጥ፣ መመርመርና ተወያይቶ ማጽደቅ፣ |
| 2.4 | እ.ኤ.አ የ2024/2025 በጀት ዓመት የውጭ ኦዲተሩን ሪፖርት ማድመጥና የባንኩን የሀብትና ዕዳ ሚዛን እንዲሁም የትርፍና ኪሳራ መግለጫ ላይ ተወያይቶ ማጽደቅ፣ |
| 2.5 | እ.ኤ.አ የ2024/2025 በጀት ዓመት የባንኩን ዓመታዊ ትርፍ እና ኪሳራ ማጽደቅ ፣ |
| 2.6 | እ.ኤ.አ የ2024/2025 የዲሬክተሮች ቦርድ አባላትን ዓመታዊ የአገልግሎት ክፍያና እ.ኤ.አ የ2025/26 ወርኃዊ ክፍያ መወሰን፣ |
| 2.7 | የስብሰባውን ቃለጉባኤ ማጽደቅ፤ |

## 3. የ14ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች

| | |
|---|---|
| 3.1. | የስብሰባውን አጀንዳ ማፅደቅ፣ |
| 3.2. | የባንኩን የመመስረቻ ጽሁፍ ማሻሻል፣ |
| 3.3. | የስብሰባውን ቃለጉባኤ ማጽደቅ፤ |

## 4. ማሳሰቢያ

**4.1** በጉባኤው ላይ መገኘት የማይችሉ ባለአክሲዮኖች፣ ተወካያችሁ ስልጣን ባለው የመንግስት አካል ተረጋግጦ የተሰጠ የውክልና ሰነድ ዋናውን እና ፎቶ ኮፒ በመያዝ ወይም በንግድ ሕጉ አንቀጽ 377 መሠረት፣ ጉባኤው ከመካሄዱ ከሦስት ቀናት በፊት ባንኩ ያዘጋጀውን የውክልና መስጫ ሰነድ፣ ሰንጋተራ በሚገኘው በባንኩ ዋና መ/ቤት ሕብር ታወር 24ኛ ፎቅ የባንኩ አክሲዮን ክፍል ድረስ ቀርቦ በመፈረም ሌላ ባለአክሲዮን ለመወከል የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን፤ ሆኖም አንድ ባለአክስዮን በማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በማንኛውም ችሎታ መወከል የሚችለው አንድ ሰው ብቻ ስለመሆኑ መገንዘብ ያስፈልጋል።

**4.2** የአክስዮን ማኅበሩ ባለአክስዮኖች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በጉባኤው ላይ ለመሳተፍ ሲመጡ፣ ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸውን የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፈቃድ ዋናውንና ኮፒ በመያዝ በጉባኤው ላይ መሳተፍ ይችላሉ። እንዲሁም ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሆኑ የውጭ ሀገር ዜግነት ያላቸው የማኅበሩ ባለአክስዮኖች ትውልደ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ቀኑ ያላለፈበት መታወቂያ (ቢጫ ካርድ) ይዘው መቅረብ እንዳለባቸው በአክብሮት እናሳውቃለን።

**4.3** ውክልና ይዘው የሚገኙ ባለአክስዮኖች በውክልና ሊይዙ የሚችሉት የውክልና መጠን፣ (የራሳቸውን አክስዮን ጨምሮ) ከባንኩ የተፈረመ ካፒታል ከአሥር በመቶ ሊበልጥ አይችልም።

**4.4** በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር SBB/91/2024 አንቀጽ 20 (3) መሠረት፣የባንኩ የቦርድ አባላትና ሠራተኞች በየትኛውም የባለአክስዮኖች ስብሰባ ላይ ማንኛውንም ባለአክስዮን ወክለው መገኘት አይችሉም።

**ሕብረት ባንክ አ.ማ**
**የዲሬክተሮችቦርድ**